# በCOVID-19 ከሚከሰት ከባድ ህመም የመያዝ አጋጣሚዎ ከፍ ያለ ከሆነ አስቀድመው እቅድ ማውጣት

Plan ahead if you are at higher risk of severe illness from COVID-19

## በCOVID-19 ከሚከሰት ከባድ ህመም የመያዝ አጋጣሚዎ ከፍ ያለ ነውን?

በCOVID-19 ከሚከሰት ከባድ ህመም የመያዝ አጋጣሚዎ ከፍ ያለ ከሆነ ከመታመምዎ በፊት የጉንፋን ወይም የኢንፍሉዌንዛ ምልክቶች ካሉብዎት ምን ማድረግ እንዳለብዎ ለማወቅ አሁኑኑ ሀኪምዎን ያነጋግሩ።

### በከባድ ህመም የመያዝ አጋጣሚዎ ካላቸው ሰዎች የሚካተቱት፡

- እድሜያቸው 70 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች
- እድሜያቸው 50 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች እና ተጨማሪ ችግሮች ላለባቸው፤ ይህም ከልክ ያለፈ ውፍረት፣ የስኳር በሽታ፣ የልብና የደም ዝውውር በሽታ፣ የማይድን ስር የሰደደ የሳንባ በሽታ (መካከለኛ ወይም ከባድ አስም ወደ ውስጥ የሚገቡ ስቴሮይዶችን ለሚያስፈጋቸው ጨምሮ)፣ የነርቭ በሽታ፣ ከባድ የማይድን ስር የሰደደ የጉበት ወይም የኩላሊት በሽታ፣ ነቀርሳ/ካንሰር ወይም የታዘዘውን ክትባት በመውሰድ ወቅታዊ ያልሆኑ
- ከላይ በተዘረዘሩት ተጨማሪ የአደጋ ምክንያቶች ላለባቸው ይህም እድሜያቸው 30 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ የአቦርጅኖችና የቶሬስ ስትሬት አይላንደር ነዋሪዎች
- በማንኛውም እድሜ ገደብ ከመጠነኛ እስከ ከባድ በሽታ የመከላከል አቅም ድክመት ያላቸው ሰዎች
- ጉልህ ወይም ውስብስብ የሆነ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች
- ነፍሰ ጡር እርጉዝ ሴቶች
- የተወሳሰበ የማይድን ስር የሰደደ ችግር ያለባቸው ህጻናት።

የሚኖሩት ራቅ ብሎ በሚገኝ አካባቢ ከሆነና ለጤና ጥበቃ አገልግሎት የማግኘት አጋጣሚዎ የቀነሰ ከሆነ አሊያም በአረጋውያን እንክብካቤ መስጫ ወይም በአካል ጉዳተኛ መገልገያ ተቋም ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ እና የፀረ ቫይረስ ህክምና ወይም ተጨማሪ ድጋፍ ለማግኘት ብቃት ስላለዎት ስለዚህ ያለዎትን ችግር ከሀኪምዎ ጋር መወያየት።

በCOVID-19 ምርመራ ላይ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ለኪምዎ ይጠይቁ እና የፀረ ቫይረስ መድሃኒቶችን እና በምርመራ ውጤት COVID-19 አዎንታዊ ቫይረስ ከተገኘብዎት ታዲያ ፀረ ቫይረስ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ይመክራሉ።

የፀረ ቫይረስ መድሃኒቶች በፍጥነት እንዲሻልዎት መርዳት እንደሚችሉ እንዲሁም በተቻለ ፍጥነት ቀደም ብሎ መውሰዱ በተሻለ ሁኔታ ይሰራሉ።

ማንኛውም የጤና ችግር ካለብዎት እና የቋንቋ ድጋፍ የሚያስፈልግዎት ከሆነ ለTIS በስልክ 131 450 ይደውሉ እና ለNational Coronavirus Helpline (አገር አቀፍ ኮሮናቫይረስ እርዳታ መስመር) በስልክ 1800 020 080 ተጠቅሞ እንዲያገናኝዎት መጠየቅ።

**ለበለጠ መረጃ በድረገጽ www.nsw.gov.au ላይ ማየት።**


© NSW Health June 2023.